የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# ከሕጋዊ እና ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማዕቀፍ ውጪ ሲንቀሳቀሱ የቆዩ የፖለቲካ ቡድኖችን በልዩ ሁኔታ የመመዝገቢያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 25/2016

ከሕጋዊ እና ሰላማዊ የፖለቲካ ማዕቀፍ ውጪ ሲንቀሳቀሱ የቆዩ የፖለቲካ ቡድኖች በኢትዮጵያ ምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 1332/2016 መሰረት በሰላማዊ መንገድ የፖለቲካ እንቅስቃሴውን ለማከናወን እና ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማበርከት በሕጋዊ የፖለቲካ ፓርቲነት በልዩ ሁኔታ ለመመዝገብ ሊሟሉ የሚገቡ መስፈርቶችን እና የልዩ ክትትል ሂደቶችን መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7 (11) እና የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 65 (9) መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### አንቀጽ 1፡ አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ " ከሕጋዊ እና ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማዕቀፍ ውጪ ሲንቀሳቀሱ የቆዩ የፖለቲካ ቡድኖችን በልዩ ሁኔታ የመመዝገቢያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 25/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### አንቀጽ 2፡ ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1. **"የተሻሻለው አዋጅ"** ማለት የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 1332/2016 ነው።
2. **"አዋጅ"** ማለት የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር. 1162/2011 ነው።
3. **"ቦርድ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 መሰረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው።
4. **"የሚመለከተው የመንግስት አካል"** ማለት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፍትህ ሚኒስቴር ነው።
5. **"በልዩ ሁኔታ የተመዘገበ ፓርቲ"** ማለት ከሕጋዊ እና ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውጪ ሲንቀሳቀስ የቆየ የፖለቲካ ቡድን ከሚመለከተው የመንግስት አካል ተገቢውን ማረጋገጫ የተሰጠው እና በሰላማዊ መንገድ የፖለቲካ እንቅስቃሴውን ለማከናወን እና ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማበርከት በሕጋዊ የፖለቲካ ፓርቲነት ለመመዝገብ ሊሟሉ የሚገቡ መስፈርቶችን አሟልቶ በልዩ ሁኔታ በፖለቲካ ፓርቲነት ተመዝግቦ ልዩ የምዝገባ ሰርተፍኬት የተሰጠው ማለት ነው።
6. **"ጉልህ የሕግ ጥሰት ማለት"** በዚህ መመሪያ አንቀጽ 16 ላይ የተዘረዘሩትን ግዴታዎች ጥሶ መገኘት፤፤ በማጭበርበር ወይም እያወቀ ወይም ማወቅ እየተገባው አሳሳች መረጃ ለቦርዱ ማቅረብ፤ ከሙስና ጋር ተያያዥነት ያላቸው የወንጀል ድርጊቶች እና የማጭበርበር ድርጊቶችን መፈጸም፤ በቦርዱ የተሰጡ ውሳኔዎች፣ ትዕዛዞች እና መመሪያዎችን አለማክበርን የሚያጠቃልሉ ድርጊቶች ማለት ነው።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

7. የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በአዋጁ እና በተሻሻለው አዋጅ ላይ የተሰጡ ለዚህ መመሪያ አግባብነት ያላቸው ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 3፡ የተፈጻሚነት ወሰን**

1. ይህ መመሪያ ከሕጋዊ እና ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማዕቀፍ ውጪ ሲንቀሳቀስ የቆየ የፖለቲካ ቡድን የኃይል እና አመጽ ተግባሩን በማቆም ሕገ መንግስታዊ ስርዓቱን በማክበር በሕጋዊ እና ሰላማዊ መንገድ ለመንቀሳቀስ መስማማቱ በሚመለከተው የመንግስት አካል ተረጋግጦ በልዩ ሁኔታ የሚመዘገብ የፖለቲካ ፓርቲ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
2. በዚህ መመሪያ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ እንደ አግባብነቱ "በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ተመዝግበው የሚገኙ የአገር አቀፍና የክልል ፓርቲዎች ማሟላት ያለባቸውን ግዴታዎች ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 3/2012" ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 4፡ የጾታ አገላለጽ**

በዚህ መመሪያ በአንዱ ፆታ የተደነገገው አነጋገር የሌላኛውን ፆታም ያካትታል፡፡

**አንቀጽ 5፡ ዓላማ**

ይህ መመሪያ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. የፖለቲካ ፓርቲ በልዩ ሁኔታ ምዝገባን፣ አሰራር እና ሂደትን መወሰን እና ማስፈፀም፤
2. የአመጽ ተግባርን በማቆም በልዩ ሁኔታ የሚመዘገቡ ፖለቲካ ፓርቲዎች ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፤
3. በልዩ ሁኔታ የሚመዘገቡ ፖለቲካ ፓርቲዎች ሕገ መንግስታዊ ስርዓቱን በማክበር እንዲንቀሳቀሱ ማስቻል፤
4. ከምዝገባው በኋላ በሚኖሩት ሁለት ዓመታት ቦርዱ የሚያከናውን የክትትል እና ቁጥጥር ማዕቀፍ ለመዘርጋት እና በግልፅ እንዲቀመጥ ማስቻል ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## በልዩ ሁኔታ ምዝገባ ተፈጻሚ የሚሆንበት አሰራር

### አንቀጽ 6፡ በልዩ ሁኔታ ለመመዝገብ የሚቀርቡ ሰነዶች

1. በተሻሻለው አዋጅ መሰረት በልዩ ሁኔታ ለመመዝገብ የሚፈልግ የፖለቲካ ቡድን የሚከተሉትን ሰነዶች አሟልቶ መቅረብ ይኖበታል፡-

   ሀ/ በልዩ ሁኔታ ለመመዝገብ የቀረበ ማመልከቻ፤

   ለ/ የፖለቲካ ፓርቲ ፕሮግራም፤

   ሐ/ የፖለቲካ ፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ፤

   መ/ የፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊዎች ስምና አድራሻ፣

   ሠ/ የፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊዎች በኃላፊነት ለመስራት መስማማታቸውን በፊርማቸው ያረጋገጡበት ሰነዶች፤

   ረ/በተሻሻለው አዋጅ አንቀጽ 2(1) መሰረት ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም በሰላማዊ እና ሕጋዊ መንገድ ለመንቀሳቀስ መስማማቱን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ መቅረብ ይኖርበታል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር(1)(ረ) መሰረት ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም የሚቀርበው ማረጋገጫ በፖለቲካ ቡድኑ ወይም በሚመለከተው የመንግስት አካል አማካኝነት ለቦርዱ ሊቀርብ ይችላል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 1(ሠ) መሰረት የቀረበውን የኃላፊዎች ዝርዝር እና ያላቸውን ኃላፊነት መቀየር የሚቻለው የፖለቲካ ቡድኑ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 መሰረት በሚያደርገው ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ አማካኝነት ብቻ ይሆናል።

### አንቀጽ 7፡ መስፈርት ያለማሟላት ውጤት

1. የፖለቲካ ቡድኑ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 6 ላይ የተመለከቱትን ሰነዶች አሟልቶ ያላቀረበ እንደሆነ እንደአስፈላጊነቱ እንዲያሟላ ቦርዱ ሊጠይቅ ይችላል ።
2. የፖለቲካ ቡድኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 በተመለከተው መሰረት ሰነዶችን እንዲያሟላ ቦርዱ ሲጠይቅ ጥያቄው በደረሰው በ5 ቀናት ውስጥ አሟልቶ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት።

### አንቀጽ 8፡ ልዩ የምዝገባ ሰርቲፊኬት ስለመስጠት

1. ቦርዱ ከላይ በአንቀጽ 6 የተዘረዘሩት ሰነዶች ሲቀርቡለት ሰነዶቹ ተሟልተው መቅረባቸውን እንዲሁም በሕግ የተመለከቱ ዝቅተኛ መስፈርቶች መሟላታቸውን ቅድመ ማጣራት በማድረግ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ የፖለቲካ ቡድኑን በልዩ ሁኔታ በመመዝገብ ልዩ የምዝገባ ሰርቲፊኬት ይሰጣል፡፡
2. በልዩ ሁኔታ የተመዘገበ ፓርቲ ልዩ የምዝገባ ሰርቲፊኬቱን ካገኘ በኋላ በአዋጁ ፣በተሻሻለው አዋጅ እና እነዚህን አዋጆች ተግባራዊ ለማድረግ የወጡ መመሪያዎችን፣ ደንቦችን፣ የቦርዱን ውሳኔዎችና ትዕዛዞች የማክበርና የመፈፀም ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## ከልዩ ምዝገባ በኋላ የሚከናወኑ ተግባራት እና ልዩ ክትትል

## ንዑስ ክፍል አንድ

## ከልዩ ምዝገባ በኋላ በመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት የሚከናወኑ ተግባራት እና ልዩ ክትትል

### አንቀጽ 9፡ ለምዝገባ የቀረቡ ሰነዶች ላይ የሚደረግ ማጣራት

1. ቦርዱ በልዩ ሁኔታ የተመዘገበው ፓርቲ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 መሰረት ፓርቲው ያቀረባቸው የፖለቲካ ፓርቲ ሰነዶች ይዘት አግባብነት ካላቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች፣አዋጁን ለማስፈፀም ቦርዱ ካወጣቸው መመሪያዎች እና ከተሻሻለው አዋጅ ጋር የተጣጣሙ ስለመሆኑ በተሻሻለው አዋጅ አንቀጽ 3 ንዑስ ቁጥር (2) (ሀ) መሰረት ተገቢውን ዝርዝር ማጣራት ያደርጋል፡፡
2. በልዩ ሁኔታ የተመዘገበው ፓርቲ ባቀረባቸው ሰነዶች ላይ በሚደረገው የማጣራት ሂደት በቀረቡት ሰነዶች ላይ ቦርዱ ለፓርቲው ማስተካከያ እንዲያደርግ ወይም ማብራሪያ እንዲሰጥበት ሊያዝ ይችላል፡፡ ፓርቲው ማስተካከያውን ወይም ማብራሪያውን ቦርዱ በሚያስቀምጠው ቀነ-ገደብ ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 10፡ የፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ ይዘት

በልዩ ሁኔታ የተመዘገበ ፓርቲ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ ቁጥር(ሐ) የሚያቀርበው የመተዳደሪያ ደንብ በአዋጁ አንቀጽ 74 በተደነገገው የፖለቲካ ፓርቲ የመተዳደሪያ ደንብ አቀራረብ መሰረት የሚከተሉትን ጉዳዮች የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ማካተት አለበት፡-

1. የአባላት ቅበላ እና ስንብት ሁኔታ፤

2. የፖለቲካ ፓርቲው ልዩ ልዩ አካላት የሚመረጡበት ሥርዓት፣ የአገልግሎት ዘመናቸው እና የስራ ኃላፊነታቸውን፤

3. አባላት የሚከፍሉት የአባልነት መዋጮ ዓይነት፤

4. የፖለቲካ ፓርቲው የጠቅላላ ጉባዔ አባላት እንደሁኔታው በአዋጁና አዋጁን ተከትሎ በወጣው መመሪያ መሠረት አገር አቀፍ ፓርቲ ከሆነ ቢያንስ 500 አባላት፣ የክልል ፓርቲ ከሆነ ቢያንስ 200 አባላት በማድረግ የሚወስን ድንጋጌ፤

5. የፖለቲካ ፓርቲው ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ቢያንስ በሦስት ዓመት አንድ ጊዜ መካሄድ ያለበት መሆኑን የሚገልጽ ድንጋጌ፤

7. የፓርቲው ቅርንጫፎች አወቃቀርና አሠራርን ጨምሮ የፓርቲውን መዋቅራዊ አደረጃጀትና የሥልጣን ተዋረድ፤

8. የፓርቲውን ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ የሚፈልጉ ጉዳዮችን ዝርዝር፤

9. የፖለቲካ ፓርቲው ከሌላ ፓርቲ ወይም ፓርቲዎች ጋር ውህደት፣ ቅንጅት ወይም ግንባር የሚፈጥርበት፣ እንዲሁም ፓርቲው የሚፈርስበትን የውሳኔና የድርጊት ሂደቶች የያዙ ድንጋጌዎች፤

10. የፓርቲው አባላት ለአገር አቀፍና በየደረጃው ላሉ አገራዊ ምርጫዎች እጩ ሆነው የሚቀርቡበት ሥርዓት፤

11. የፖለቲካ ፓርቲው የሰው ኃብት፣ የፋይናንስ እና የኦዲት አስተዳደር ሥርዓት አሰራር፣

12. የፓርቲውን ገንዘብና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት፣ የገቢ ማስገኛ አሰራር እና በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ለመወሰን ሥልጣን ያለውን አካል ወይም ኃላፊን የሚገልጽ ድንጋጌ፤

13. የፖለቲካ ፓርቲውን የውስጥ አለመግባባቶች አፈታት ሥርዓት፤

14. የፓርቲው አመራሮችና በየደረጃው ያሉ ኃላፊዎች አመራረጥ ግልጽ፣ ነጻና ፍትሃዊ እንዲሁም በሚስጢር በሚሰጥ ድምጽ መንገድ የሚመረጡ መሆናቸውን የሚገልጽ ድንጋጌ ማካተት ይኖርበታል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

## አንቀጽ 11፡ የአባላት ዝርዝርን ስለማቅረብ

1. በልዩ ሁኔታ የተመዘገበ ፓርቲ የአባላቱን ዝርዝር ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት የመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት ውስጥ ቦርዱ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር (1) መሰረት የቀረበው የአባላት ዝርዝር በልዩ ሁኔታ የተመዘገበው ፓርቲ የአባላቱ ቁጥር በአዋጁ ከተቀመጠው ዝቅተኛ የአባላት ቁጥር ያነሰ መሆኑን የሚያመለክት ከሆነ ቦርዱ የተጓደሉትን አባላት እንዲያሟላ ለፓርቲው ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡
3. በአዋጁ የተቀመጠውን ዝቅተኛ የአባላት ቁጥር የተጓደለበት በልዩ ሁኔታ የተመዘገበ ፓርቲ ቦርዱ በሚያስቀምጠው ቀነ-ገደብ ውስጥ የተጓደሉ አባላቱን አሟልቶ ለቦርዱ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር(1) መሰረት የሚቀርብ የአባላት ዝርዝር በአዋጁ እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ተመዝግበው የሚገኙ የአገር አቀፍና የክልል ፓርቲዎች ማሟላት ያለባቸውን ግዴታዎች ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 3/2012 የተቀመጡ የአባላት ዝርዝር አቀራረብ ይዘቶችን የተከተለ መሆን ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 12፡ ጠቅላላ ጉባኤ

1. በልዩ ሁኔታ የተመዘገበ ፓርቲ ለምዝገባ ለቦርዱ ያቀረባቸው እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 መሰረት ተጣርቶተቀባይነት ያገኙ የፖለቲካ ሰነዶቹን በልዩ ሁኔታ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ ጠቅላላ ጉባዔ በማድረግ ማፀደቅ እና አመራሮቹንም በዚሁ በፀደቀው ደንብ መሰረት ማስመረጥ ይኖርበታል፡፡
2. በልዩ ሁኔታ የተመዘገበ ፓርቲ ጠቅላላ ጉባኤ የሚያደርግበትን ቀን ሲወስን ቢያንስ ከሃያ አንድ ቀን አስቀድሞ ለቦርዱ ማሳወቅ እና የቦርዱ ተወካዮች በጉባዔው ላይ በታዛቢነት እንዲገኙ ጥሪ መቅረቡን ማረጋገጥ አለበት፡፡
3. በልዩ ሁኔታ የተመዘገበው ፓርቲ የሚያደርገው የጠቅላላ ጉባኤ አጠራር እና ዝግጅት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9(1) መሰረት በቦርዱ ተቀባይነት ባገኘው የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት መሆን ይኖርበታል፤ ቦርዱም ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር(1) መሰረት የስድስት ወር የጊዜ ገደቡ ሳይጠናቀቅ በፊት ጠቅላላ ጉባዔ የሚደረግበትን ቀን ፓርቲው ያልወሰነ ወይም ያላሳወቀ እንደሆነ ቦርዱ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት በማስገባት ጠቅላላ ጉባዔ የሚያደርግበትን ቀን ለፓርቲው ያሰውቃል።

**አንቀጽ 13፡ የመጀመሪያው ስድስት ወራት ላይ ቦርዱ የሚያደርገው ክትትል እና ሪፖርት አቀራረብ**

1. በልዩ ሁኔታ የተመዘገበ ፓርቲ በመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት ፓርቲው በሕጋዊ እና ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ሽግግር ለማድረግ እንዲያስችሉት እየተከናወኑ ስላሉ ሥራዎች በየወሩ ለቦርዱ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል።
2. በሚቀርበው ሪፖርት ላይ በተለይም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 መሰረት ተስተካክለው እንዲቀርቡ ወይም ማብራሪያ የተጠየቀባቸው ጉዳዮች ካሉ ይህን አስመልክቶ የተከናወኑ ሥራዎችን እንዲሁም በዚህ መመሪያ አንቀፅ 12 መሰረት በሚደረገው ጠቅላላ ጉባዔ ከሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ የሚወሰኑ ውሳኔዎች አፈፃፀምን ማካተት ይኖርበታል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር(1) መሰረት በቀረበው ሪፖርት ላይ ቦርዱ አስፈላጊውን ግምገማ በማድረግ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ግብረ-መልሱን ለፓርቲው መላክ ይኖርበታል።
4. በልዩ ሁኔታ የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ እንዲፈፅም በቦርዱ የተሰጡትን ትዕዛዞችና መመሪያዎች ማክበሩን በየጊዜው ክትትል ያደርጋል።

**ንዑስ ክፍል ሁለት**

**<u>በቀሪ የአንድ ዓመት ከስድስት ወር ጊዜያት የሚከናወኑ ተግባራት እና ልዩ ክትትል</u>**

**አንቀጽ 14፡ የልዩ ሪፖርት አቀራረብ**

1. በልዩ ሁኔታ የተመዘገበ ፓርቲ የመጀመሪያው ስድስት ወራት ከተጠናቀቀ በኋላ በሚኖረው ቀሪ የአንድ ዓመት ከስድስት ወር ልዩ የክትትል ጊዜ ውስጥ በአዋጁ፣ በተሻሻለው አዋጅ፣በዚህ መመሪያ፣ እንዲሁም ተፈጻሚነት ባላቸው ሌሎች የቦርዱ መመሪያዎች መሰረት የተጣለበትን ግዴታዎች ለመወጣት እያከናወነው ስላለው ተግባራት በየሦስት ወሩ ለቦርዱ ልዩ ሪፖርት ማቅረብ አለበት።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር(1) መሰረት በቀረበው ሪፖርት ላይ ቦርዱ አስፈላጊውን ግምገማ በማድረግ ሪፖርቱ በደረሰው በአስር የሥራ ቀናት ውስጥ ግብረ-መልሱን ለፓርቲው መላክ ይኖርበታል።

3. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚቀርቡ ልዩ ሪፖርቶች ሊያካትቱት የሚገቡ ጉዳዮችን በተመለከተ መነሻ የሚሆን ቅጽ በማዘጋጀት ሊልክ ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር(1) መሰረት በልዩ ሁኔታ በተመዘገበ ፓርቲ የሚቀርበው ልዩ ሪፖርት በአዋጁ እና አዋጁን ለማስፈፀም በወጡ መመሪያዎች መሰረት እንደማንኛውም የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ ለቦርዱ ማቅረብ የሚጠበቅበትን የሪፖርት አይነቶች እና ይዘታቸውን ግዴታነት ቀሪ የሚያደረግ አይደለም፡፡

**አንቀጽ 15፡ ቦርዱ ክትትል የሚያደርግባቸው መንገዶች**

1. ቦርዱ በልዩ ሁኔታ የተመዘገበ ፓርቲን ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴን በተመለከተ በዚህ መመሪያ በአንቀፅ 14 መሰረት ከፓርቲው ከሚቀርብለት ወቅታዊ ልዩ ሪፖርት በተጨማሪ በሚከተሉት መንገዶች መረጃዎችን በመሰብሰብ የሁኔታ ትንተና ሊያከናውን ይችላል፡-

   ሀ) በመገናኛ ብዙሃን በሚሰራጩ መረጃዎች የህትመት እና የበይነ መረብን ጨምሮ የሚዲያ ዳሰሳ በማድረግ ከሚገኙ መረጃዎች፤

   ለ) በማህበራዊ ትስስር ገፆች ላይ በሚደረግ ክትትል እና ትንተና፤

   ሐ) እንደ አስፈላጊነቱ የቦርዱ የባለሙያዎች ቡድን በሚያደርገው የመስክ ምልከታ ውጤት፤

   መ) በአካባቢው ላይ ከሚንቀሳቀሱ በቦርዱ የተመዘገቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች፤

   ሠ)ከመንግስት ተቋማት

   ረ) ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፤

   ሰ) ከሀገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ተቋማት ከሚያወጡት ሪፖርቶች፤

   ሸ) ከምርመራ እና የፍርድ ቤት መዛግብት፤

   ቀ) ከጥናት እና ምርመር ሥራ ውጤቶች፤

   በ) በተለያየ መንገድ ከህዝብ ከሚሰበሰቡ አስተያየቶች መረጃዎችን ሊሰበስብ ይችላል፡፡

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር(1) እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ ፓርቲው ሕጋዊ እና ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማዕቀፍ ውስጥ ስለመኖሩ አመቺ ነው ባላቸው መንገዶች ወይም ቦርዱ ጠቃሚ ነው



የኢትዮጵያ ብሔራዊ ... NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ብሎ ከሚያምንባቸው ማንኛውም የመረጃ ምንጮች መረጃዎችን ሊሰበሰብ እና ሊያረጋግጥ ይችላል።

3. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር(1) መሰረት ለሚሰበስባቸው መረጃዎች ማንኛውም የመንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ ይኖርባቸዋል።

## ክፍል አራት

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

### አንቀጽ 16፡ ኃይልን መሰረት ያደረገ የአመጽ ድርጊት ውስጥ ያለመሳተፍና ከአዋጆችና ከቦርዱ ውሳኔዎች ውጭ ያለመፈፀም ግዴታዎች

በአዋጁ እና በተሻሻለው አዋጅ እንዲሁም በሌሎች ሕጎች የተቀመጡ ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም በልዩ ሁኔታ የተመዘገበ ፓርቲ እና አባላቱ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖርባቸዋል፡-

1. በማንኛውም መልኩ ከኃይል ድርጊት ወይም ከአመጽ ተግባር ከመሳተፍ የመቆጠብ፤
2. አለመግባባቶችን በሰለማዊ መንገድ ከመፍታት ባለፈ የኃይል ድርጊትን እንደ አማራጭ እንደሚጠቀም ከመግለፅ ወይም ከማስፈራራት የመቆጠብ፤
3. በይፋም ይሁን በስውር በግለሰቦች ላይ ወይም በቡድኖች ላይ ጥላቻን፣ አመጽን ፣ፍርሃትን ወይም ግጭትን ከሚቀሰቅሱ ንግግሮች ወይም ተግባራት የመቆጠብ፤
4. በማንኛውም መልኩ ለአመጽ የሚጋብዝና በግለሰቦች ወይም ቡድኖች ላይ ስጋትን የሚጭር ቋንቋን ወይም ሐሰተኛ መረጃዎችን በመገናኛ ብዙሃን፣ በህትመት ውጤቶች፣ በማህበራዊ የትስስር ገፆች ወይም በሌሎች መንገዶች ከማሰራጨት የመቆጠብ እና
5. አመራሮቹ እና አባላቱ ኃይልን መሰረት ያደረገ የአመጽ ተግባር ውስጥ እንዳይሳተፉ ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር የማድረግ ግዴታ ይኖርባቸዋል።
6. በአዋጁ እና በተሻሻለው አዋጅ፣ እነዚህን አዋጆች ተከትለው የወጡ መመሪያዎች ፣የቦርዱን ውሳኔዎችና ትዕዛዞች የማክበር እና የመፈፀም ግዴታ አለበት።

### አንቀጽ 17፡ ማስጠንቀቂያ ስለመስጠት

1. በልዩ ሁኔታ የተመዘገበ ፓርቲ በተሻሻለው አዋጅ እና በዚህ መመሪያ መሰረት ቦርዱ በሚያደረገው የሁለት ዓመት ልዩ የክትትል ጊዜ ውስጥ በአዋጁ ፣ በተሻሻለው አዋጅ እና እነዚህ አዋጆችን

ለማስፈፀም የወጡ መመሪያዎችን፣ የቦርዱን ውሳኔዎችንና ትዕዛዞችን የጣሰ እንደሆነ የእርምት እርምጃ እንዲወስድ ቦርዱ ለፓርቲው የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር(1) መሰረት ማስጠንቀቂያ የደረሰው በልዩ ሁኔታ የተመዘገበ ፓርቲ ወዲያውኑ የእርምት እርምጃ በመውሰድ ለቦርዱ የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

**አንቀጽ 18፡ ስለማገድ**

1. በልዩ ሁኔታ የተመዘገበ ፓርቲ ጉልህ የህግ ጥሰት ስለመፈጸሙ ቦርዱ ሲያረጋግጥ እና አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን ፓርቲው ምንም አይነት የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዳይሳተፍ እስከ ሶስት ወር ሊያግደው ይችላል።
2. በልዩ ሁኔታ የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር (1) መሰረት ለእግድ ምክንያት የሆነውን ጥሰት ካስተካከለና ስለመስተካከሉ ቦርዱ ሲያረጋግጥ እግዱን ሊያነሳ ይችላል።

**አንቀጽ 19፡ ስለመሰረዝ**

1. ቦርዱ ከዚህ ተከትሎ በተዘረዘሩ ምክንያቶች በልዩ ሁኔታ የተመዘገበን ፓርቲ ከምዝገባ ሊሰርዝ ይችላል፡-

ሀ. በክትትል ወቅት የእርምት እርምጃ እንዲወስድ ከቦርዱ በተሰጠው ግብረመልስ መሰረት የእርምት እርምጃ ካልወሰደ፤

ለ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 16 ስር የተመለከተውን ግዴታ ተላልፎ ከተገኘ፤

ሐ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 18 መሰረት የታገደ በልዩ ሁኔታ የተመዘገበ ፓርቲ በተሰጠው የእግድ ጊዜ የእርምት እርምጃ ካልወሰደ፤

መ. በአዋጁ አንቀጽ 98 መሰረት ፓርቲን ከምዝገባ ስለመሰረዝ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ፈፅሞ ከተገኘ፤

ሠ. በተሻሻለው አዋጅ አንቀጽ 3 መሰረት የተቀመጡ ግዴታዎቹን ያልተወጣ እና ጉልህ የሕግ ጥሰት የፈፀመ እንደሆነ ቦርዱ ከምዝገባ ይሰርዘዋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

2. በአዋጁ አንቀጽ 99 የተመለከተው የፖለቲካ ፓርቲ መሰረዝ ወይም መፍረስ ውጤት በልዩ ሁኔታ ተመዝግቦ የመሰረዝ ውሳኔ የተሰጠበት ፓርቲ ላይም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 20: ስለ መሰማት መብት**

ቦርዱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 18 እና 19 መሰረት በልዩ ሁኔታ የተመዘገበ ፓርቲ ማገድ ወይም መሰረዝን አስመልክቶ በሚወስናቸው ውሳኔዎች ላይ ፓርቲው መከላከያውን አቅርቦ እንዲያሰማ እድል ይሰጠዋል፡፡

**አንቀጽ 21፡ የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ወይም አካል የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ለማድረግ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 22፡ ተፈፃሚነት የሌላቸው መመሪያዎች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

**አንቀጽ 23፡ መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በቦርዱ ከፀደቀበት ሐምሌ 25 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ሜላትወርቅ ኃይሉ**

**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ**

**ሰብሳቢ**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA